በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፭


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሐምሌ ፲፯ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**

# <u>እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩</u>

## <u>መግቢያ</u>

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክ መላውን የንስሐ ጉዞ በግልጽ የሚያሳየን ኑዛዜ ነው፡፡
- ተነሳሒው (ንስሐ የሚገባው ሰው) ከሁሉ አስቀድሞ በደሉን በእግዚአብሔር ፊት ይናዘዝና በመቀጠልም በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ በተመረጠውና በተሾመው ካህን ፊት ቀርቦ ይናዘዛል፡፡
- እንግዲህ ተነሳሒው ከኑዛዜው በፊት በሚከተሉት መንገዶች መራመድ ይገባዋል፡-
    1. ውድቀቱንና ስኬቱን በሚመረምርበት ሁኔታ ውስጥ መገኘት፣
    2. በበደሉ ምክንያት እግዚአብሔር በአምሳሉና በአርአያው የፈጠረውን መልክ አበላሽቷልና ስለዚሁ ድካም ራሱን መውቀስ፣
    3. በእግዚአብሔር ፊት ቀርቦ ንስሐ መግባት፣ ይቅርታን መጠየቅና መንፈስ ቅዱስ በምናደርገው መንፈሳዊ ጥረት ያግዘን ዘንድ ልመናን ማቅረብ፣
    4. ‹‹አባቴ ሆይ በሰማይና በምድር በፊትህ በደልሁ›› *<u>ሉቃ 15፡18፡፡</u>* ብለን ወደ ቤ/ክ በመምጣት በካህኑ (በንስሐ አባታችን) ፊት ቀርበን መናዘዝ፤ ይህን በማድረጋችንም ካህኑ ምን ማድረግ እንዳለብን ይመራንና ይመክረን ዘንድ እድል እናገኛለን፡፡
- ብዙዎች እንዴት መናዘዝ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ያለ ንስሐ ይናዘዛሉ ወይም ያለ ኑዛዜ ለንስሐ ይቀርባሉና ስለ ንስሐና ኑዛኔ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ይህ ትምህርት ተዘጋጅቷል፡፡ እግዚአብሔር ስለ ስሙ እያንዳንዱን ሥራችንንና አገልግሎታችንን ይባርክልን፡፡ አሜን፡፡
- ለኑዛዜ ስንቀርብ በሚከተሉት መንገዶች ሆነን መናዘዝ ከሁላችንም ይጠበቃል፡፡

# <u>እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩</u>

## <u>በመስማት ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር</u>

1. ፍትወተ ሥጋን አስመልክቶ የሚወሩ ወሬዎችን ሰምተን እናውቃለን? ከሰማንም በኋላ በወሬው ተማርከን፣ ወሬውንም በልባችን አሳድረን በቆይታ ፍላጎታችንን እንዲቀሰቀስበት በአእምሮአችን አኑረነው በመቀጠልም ይህኑ ድምጽ በመስማት የተደሰትንበት ወይም የተዝናናንበት አጋጣሚ ካለ በኑዛዜ ጊዜ መናዘዝን አንርሳ፤
2. የግላቸውን ወሬ የሚያወሩ ሰዎችን ለማዳመጥ ትኩረት ሰጥተን ከተከታተልን፣ የሚሠሩትንና የሚፈልጉትን ብሎም የሚያስቡትን ሳይቀር በመሰለል ድርጊት ተሳትፈን እንደሆነ አንርሳ፤
3. `
4. ሰው ሲከሰስና ሲወቀስ ብሎም ሲወገዝ ጉዳዩ ባይመለከተን፣ በንግግሩና ውይይቱ ውስጥ ባንኖርበትም የዚያን ሰው ውርደት በመስማት ተደስተን እንደሆነ አንርሳው፣
5. የሥጋ ፍትወታችንን የሚያነሳሱ ወይም መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚያቀዘቅዙ ሙዚቃዎችን ሰምተን እንደሆነ ስንናዘዝ አንርሳ፣
6. ሌሎች ሰዎች በከንቱ ውዳሴ ሲያወድሱን በመስማት ተደስተን እንደሆነም አንርሳ፣
7. ስንወቀስና ስንተች አዝነን ወይም ቅር የመሰኘት ምልክት አሳይተን እንደሆነ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት::›› <u>*ያዕ1:2-3::*</u> ይላልና ስለዚህም ድካማችን እንናዘዝ፣

# እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩

## በመስማት ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር

8. የእግዚአብሔርን ጥሪ ከመስማት ቸል ብለን የዓለምን ነገር ወደ መስማት አዘንብለን እንደሆነም አንርሳ፣ ‹‹በምድረ በዳ እንደ ተፈታተኑት እንዳስቈጡት ጊዜ፥ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ።›› ***መዝ 94(95)፡8፡፡*** ይለናልና፡፡
9. እንደ ዮሴፍ ወንድሞች በክፉ የሚመክሩ ሰዎችን ምክር በመስማማት ሰምተን እንደሆነም አንርሳ፡፡ ***ዘፍጥ 37፡4-ፍጻሜ***፣
10. በቅዳሴ ወይም በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሰዓት በተመስጦ የማንከታተል ትኩረት የማንሰጥ ከሆንን መናዘዝን አንርሳ፡፡ ***ኢሳ 30፡15፣ የሐዋ 21፡40፣ ቀዳ ሰተ 4፡10-12፣ ካል ተሰ 3፡12፣***
11. የድሆችን ጩኸት ከመስማት ጆሮአችንን መልሰን እንደሆነ ስንናዘዝ አንርሳ፣ ‹‹የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፥ እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰማለትምና።›› ***ምሳ 21፡31፡፡***
12. ወደ ንስሐ በተለያየ መንገድ የሚጠራንን የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ጥሪ ቸል ብለን እንደሆነ ለመናዘዝ አንርሳ፣

## በመናገር (በነቢብ) ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር

1. ጌታችን ‹‹በመንድሙ ላይ የሚቆጣ ፍርድ ይገባዋል›› ***ማቴ 5፡22፡፡*** እንዳለ ወንድሞቻችንን/ እህቶቻችንን በመሳደባችን የሚጠብቀን ፍርድ ነውና እንናዘዘው፣
2. መልካምነትን የያዝን አስመስለን መዋሸትን የመሰለ ክፉ ነገር የለምና እንደህም አድርገን እንደሆነ እንናዘዝ፣ ልበ አምላክ ዳዊትም ‹‹አድነኝ፥ አፉቸውም ምናምንን ከሚናገር፥ ቀኛቸውም የሐሰት ቀኝ ከሆነ፥ ከባዕድ ልጆች እጅ አስጥለኝ።›› ***መዝ 143(144)፡11፡፡*** በማለት የጸለየው እንዲህ ላለነው ነውና፡፡

# <u>እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩</u>

## <u>በመናገር (በነቢብ) ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር</u>

- አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን የተቀሩት ደግሞ ሰዎችን ይዋሻሉ፤ እግዚአብሔርን የሚዋሹም ሰዎችን ከሚዋሹ የከፉ ናቸው:: ***<u>መዝ 65(66)፡3፣ መዝ 77(78)፡36።</u>***
- ሐሰትም የዓመፅ ሁሉ (ፍርሐት፣ ስግብግብነት፣ አስመሳይነት፣ ትምክህት፣ ትዕቢት) ራስ/ዘር ናት፤ እርሱም ከዲያቢሎስ ነው ‹‹ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና። ›› ***<u>ዮሐ 8፡44።</u>***
- ሐሰት ሌላ የነቢብ ኃጢአት ወደ መሥራት ያመራል እርሱም መሐላ ነው::

3. እውነትም ሆነ አልሆነ ‹‹ፈጽማችሁ አትማሉ::›› ***<u>ማቴ 5፡34።</u>*** ስለ ተባልን ምለን እንደሆነ መናዘዝን አንርሳ፣
4. በሰዎች መካከል የተፈጠረውን መራራቅ የበለጠ ለማስፋት ስንል ሌሎች ሰዎች የተጠቀሙበትን አስነዋሪ ቃላት በመጠቀም መናገር ከፍቅር መጉደል የሚመነጭ ነውና ኑዛዜ ያስፈልገዋል::
5. የሰዎችን ግላዊ ጉዳይ ለማወቅ ያገኘነውን እድል በመጠቀም ነገራቸውን ሁሉ አቅል በማሳጣት፣ በማቃለልና ምስጢራቸውንም አውጥተን በመናገር በግል ጉዳያቸው በመፍረድ ተገኝተን እንደሆነ አንርሳ፣
6. በማፌዝ መልስ ሰጥተን ወይም ተናግረን እንደሆነም አንርሳ፡ ‹‹ የስንፍና ሐሳብ ኃጢአት ነው ሰዎች ፌዘኛውን ይጸየፉታና::›› ***<u>ምሳ 24፡9።</u>***

# እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩

## በመናገር (በነቢብ) ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር

7. ክብርና ቅንነት ጎድሎን ወይም የአንድን ሰው አነጋገር/አረማመድ... እያሳየን በነገሮች የምናፌዝ የምንቀልድ እንደሆንን መናዘዝን አንርሳ፣
8. በተራ ክርክሮች መካከል ገብተን ነገር አጋግለን እንደሆንን መናዘዝን አንርሳ፣
9. ለሰዎች ስሜትና ፍላጎት ትኩረት በመንፈግ በሚያሰቅቅ መልኩ በኃይለ ቃል ተናግረናቸው እንደሆነ እንደሆንን መናዘዝን አንርሳ፣
10. የዘፈን ግጥሞችን እያስታወስን ማንጎራጎራችን ልባችን ከዚህ ዓለም ጋር የተጣበቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ መናዘዝን አንርሳ፣
11. ቅጡ ባልታወቀ በተበላሸና በተደበላለቀ መንገድ የተናገርንበትንም አጋጣሚ አንርሳ፣
12. ክብርን ከመፈለግ የተነሣ የአንድን ሰው ሐሳብንና ንግግር ከሚገባው መጠን በላይ አጋነን አቅርበን እንደሆነም አንርሳ፣
13. እምነታችንን ክደን እንደሆነ አንርሳ፤ ይኸውም፡-
    - ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን በትክክል አለመመስከር/አለማስረዳት
    - ክርስቲያናዊ ማንነታችንን በሚገልጥ መልኩ አለመናገር (ክርስትና ስማችንን አንስተን አለመተዋወቅ)
    - እግዚአብሔርን ማማረር ስሙም የሚሰደብበትን ሥራ መሥራት ሊረሳ አይገባውም፡

# እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩

## በመናገር (በነቢብ) ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር

14. በውይይት ወቅት ሌሎችን መስማት ትተን ያለ ልክና መጠን ዝም ብለን የምናወራ ከሆን አንርሳ፣
15. በኅብረ ዝማሬ እንደ ንብ ከመዘመር ይልቅ ድምጻቸውን ለብቻቸው አጉልተው እንደሚያወጡ ሰዎች በዕድሜና በክብር ከኛ የሚበልጡ ታላላቆችን በመዝለፍና በመገሰጽ የምንደሰትና ለማስተማርም የምንደፍር ከሆን አንርሳ፣
16. ሌላው ሰው ክፉ እንዲገጥመው ወይም እንዲያገኘው የምንጸልይ እንደሆን መናዘዝን አንርሳ፣
17. በሐሰት የምንመሰክር ከሆን መናዘዝን አንርሳ፣
18. ስለራሳችን ጽድቅ የምንገልጽ/የምናወራ (ስለ ሠራነው ሥራ፣ ስለ ጠቃሚነታችን አውርተን ጎጂ ጎናችንን መደበቅ፣ የሌሎችን ምክር ፈጽሞ አለመቀበል፣ ስለ ሠራነው ስህተት ፈጽመን አለመናዘዝ፣ በምድራዊ ነገር መመካት...) ከሆን መናዘዝን አንርሳ፣
19. በቤ/ክ ጉባኤ፣ ቅዳሴ፣... ጊዜ የምንስቅ ወይም የምናወራ ከሆን መናዘዝን አንርሳ:: ሰነፎች ‹‹ደምን ለማፍሰስ እግራቸው ፈጣን ነው ጥፋትና ጉስቍልና በመንገዳቸው አለ፥ የሰላምን መንገድ አላወቁአትምና እግዚአብሔርን መፍራት በዓይናቸው ፊት የለምና።›› ***መዝ 14:6::***

# እንዴት እንናዘዝ? - ክፍል ፩

## በማየት ስለ ፈጸምነው ኃጢአት (በደል) በመናገር

1. ከሞራል አንጻር ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን መመልከት ወይም የማይመለከተንን ጥልቅ ብለን አይተን እንደሆነ ስለዚህም መናዘዝን አንርሳ፣
2. የሰዎችን ንብረት፣ ልብሶች፣ ጌጣጌጦች… ወዘተ ተመኝተን እንደሆነ መናዘዝን አንርሳ፣
3. ድሃውን በማዋረድና ባለጠጋውንና ጠቢቡን ከፍ በማድረግ ከውጪ ያለውን ብቻ በማየት ፈርደን እንደሆነ ስለዚህም አንርሳ:: ‹‹ እናንተ ግን ድሆችን አዋረዳችሁ። ባለ ጠጎቹ የሚያስጨንቁአችሁ አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤትም የሚጎትቱአችሁ እነርሱ አይደሉምን?›› ***ያዕ 2፡6***፣ ‹‹ በሰማርያ ተራራ የምትኖሩ፥ ድሆችንም የምትበድሉ፥ ችጋረኞችንም የምታስጨንቁ፥ ጌቶቻቸውንም። አምጡ እንጠጣ የምትሉ እናንተ የባሳን ላሞች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ።›› ***አሞ 4፡1፡፡***

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org